በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገቢዎች ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF REVENUES

ቀን / Date: ጥር 03 2015
ቁጥር / Ref.No: ደ/64/15

በዝርዝር ለተመለከተቱት በሙሉ

በያሉበት

ጉዳዩ:- መመሪያ ስለመላክ፤

የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ተሻሽሎ የወጣን መመሪያ ቁጥር 179/2015 ከዚህ ጋር በማያያዝ የላክን ስለሆነ በመመሪያው መሠረት እንዲፈፀም አስታውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ:-

- ለሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለታክስ ስርአርት ዘርፍ
- ለታክስ ኦኘሬሽን ዘርፍ
- ለተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ቢሮ

ገቢዎች ሚኒስቴር

Phone: +251 11 662 98 00/ 01/02/03/04/05/06/07/08 Fax: /+251 11 662 98 17
face book page: ministry of revenues. FBP: mor Ethiopia Twitter: erca@twitt
web site: http//www:erca.gov.et P.o. Box: 2559 Addis Ababa, Ethiopia

# የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ መመሪያ ቁጥር 179/2015

ጥር 2015 ዓ.ም
አዲስ አበባ

በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ መሰረት የሚፈለግበትን የታክስ ዕዳ በወቅቱ ወይም በአንድ ጊዜ መክፈል ለማይችል ታክስ ከፋይ ሚኒስቴሩ የክፍያ ጊዜ ሊያራዝም እንደሚችል የተደነገገ በመሆኑ፤

የታክስ ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዮች የክፍያ ግዴታቸውን እንዲወጡ ተገቢነት ያላቸውን ሁኔታዎች በማመቻቸት ድጋፍና እገዛ ማድረግ የሚጠበቅበት በመሆኑ፤

ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን የታክስ ዕዳ በአንድ ጊዜ መክፈል በማይችልበት ጊዜ የተራዘመ የዕዳ መክፈያ ጊዜ ስምምነት በማስገባትና ተጠያቂነት ያለው የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የሚስተናገድበትን ሁኔታ መፍጠር ተገቢ ስለሆነ፤

የገቢዎች ሚኒስቴር በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 32(2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ መመሪያ ቁጥር 179/2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈጻፀም የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፤

1/ "የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ" ማለት ማንኛውም ታክስ ከፋይ በአዋጁ መሰረት የመክፈያ ጊዜው የደረሰ ወይም በወቅቱ ያልተከፈለ የታክስ ዕዳን ለመክፈል ጊዜ እንዲራዘምለት ሲያመለክት ከመደበኛው የታክስ መክፈያ ጊዜ በተለየ ሁኔታ እንዲከፈል የሚሰጥ የክፍያ ጊዜ ነው፡፡

2/ "የክፍያ ጊዜ ስምምነት" ማለት ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን የታክስ ዕዳ በአንድ ጊዜ መክፈል ሳይችል ሲቀር ታክስ ከፋዩ እና የታክስ ባለሥልጣኑ ክፍያው የሚፈጸምበትን ጊዜ እና ሁኔታ በተመለከተ በፅሁፍ የሚያደርጉት የስምምነት ውል ነው፡፡

3/ "የታክስ ከፋዮች ምደባ" ማለት የታክስ ባለስልጣኑ መስሪያ ቤት በሚያወጣው መስፈርት የከፍተኛ ፣ የመካከለኛ እና የአነስተኛ ደረጃ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች የሚያመላክት ነው፡፡ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ብቻ ከአዲስ አበባ ውጪ ያሉ ቅ/ጽ/ቤቶች አነስተኛ ደረጃ ተብለው



ከበረ ለበበ መንገሻ የሚኒስቴር ሕግ አማካሪ

ይወሰዳሉ፡፡

4/ “ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት” ማለት በተወሰነ አካባቢ በተከሰተ የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ ማለትም ጦርነት፣ ዝርፊያ፣ ጐርፍ፣ ቃጠሎ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ መብረቅ፣ ተምች ወይም ሌላ ተመሣሣይ ክስተት ሲያጋጥም ነው፡፡

5/ “ሀብቱ በዕዳ የተያዘበት” ማለት የታክስ ዕዳ ለበት ታክስ ከፋይ የሚንቀሳቀስ ወይም የማየንቀሳቀስ ሀብት ለታክስ ዕዳ ማካካሻነት የታክስ ባለስልጣኑ ለመሸጥ የተረከበው ማለት ነው፡፡

6/ “የታክስ ዕዳ” ማለት በታክስ ህጎች መሰረት በመክፈያ ጊዜው ያልተከፈለ ታክስ ሲሆን፣ ወለድ እና አስተዳደራዊ መቀጫዎችን ይጨምራል፡፡

7/ “ዋስትና” ማለት የታክስ ክፍያ ጊዜ እንዲራዘምለት የጠየቀ ታክስ ከፋይ በታክስ ባለስልጣኑ ሲጠየቅ የሚያቀርበው የባንክ ወይም የንብረት ዋስትና ነው፡፡

8/ “የማይነሳ አስተዳደራዊ ቅጣት” ማለት በታክስ አስተዳደር ቅጣት አነሳስ መመሪያ መሠረት እንዲነሳ ያልተፈቀደው እና የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነቱ አካል የሆነው ተከፋይ አስተዳደራዊ ቅጣት ነው፡፡

9/ "ያልተከፈለ ታክስ” ማለት በመክፈያ ቀን ወይም የታክስ ባለስልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 32 የተመለከተውን የታክስ መክፈያ ጊዜ ያራዘመ ከሆነ በተራዘመው ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለ ቀሪ ታክስ ማለት ነው፡፡

10/ “የታክስ ስሌት” ማለት የራስ ታክስ ስሌት፤ በግምት የሚከናወን የታክስ ስሌት፣ የስጋት ታክስ ስሌት፣ የተሻሻለ ታክስ ስሌት፣ አስተዳደራዊ ቅጣት ፣ ወለድ ወይም በታክስ ህግ መሰረት የሚደረግ ማንኛውም ስሌት ነው፡፡

11/ “የራስ ታክስ ስሌት” ማለት በታክስ ባለሰለጣኑ በጸደቀው ቅጽ መሰረት ታክሱን የማስላት ግዴታ ባለበት ታክስ ከፋይ የተዘጋጀ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ማለት ነው፡፡

12/ ”አዋጅ” ማለት የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ነው፡፡

13/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ማለት ነው፡፡

14/ "የታክስ ባለስልጣን" ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ሲሆን ፣ የአዲስ አበባ ከተማ እና የድሬዳዋ አስተዳደር የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችን ይጨምራል፡፡

15/ በዚህ መመሪያ ውስጥ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላትና ሀረጎች በፌደራል ገቢ ግብር አዋጅና ደንብ እንዲሁም በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡



አበራ አበበ
የማኔጅመንት ... ሕግ

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

የጡረታ መዋጮ እና የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ክፍያን ሳይጨምር በወቅቱ መከፈል ያለበትን ታክስ ወይም የመክፈያ ጊዜው ያለፈበትን ታክስ በአንድ ጊዜ መክፈል በማይችል እና የክፍያ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ በሚጠይቅ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት ስለሚፈቀድባቸው ወይም ስለሚከለከልባቸው ሁኔታዎች

4. <u>የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች</u>

በዚህ መመሪያ መሰረት የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት የሚፈቀደው፡-

1/ ታክስ ከፋዩ የታክስ ዕዳውን በአንድ ጊዜ መክፈል የማይችል ሲሆን ነው፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ቢኖርም ሀብቱ እንዲያገ ዘ የዕግድ ትዕዛዝ የተላለፈበት ወይም ንብረቱ እንዲሸጥ ጨረታ የወጣበት ታክስ ከፋይ ዕዳውን ለመክፈል ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ ለዕዳው ተመጣጣኝ ሆነ የባንክ ወይም የንብረት ዋስትና ሲያቀርብ ብቻ ይሆናል፡፡፣

5. <u>የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የማይፈቀድባቸው ሁኔታዎች፡-</u>

1/ የጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት የማይፈቀድባቸው ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

(ሀ) በታክስ ማስታወቂያ (በራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ) ማቅረቢያ ጊዜ መከፈል ያለበት የታክስ ዕዳ ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ ወይም ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ገቢ መደረግ ያለበት ሲሆን ፣

(ለ) ታክስ ከፋዩ አስቀድሞ የክፍያ ጊዜ ስምምነት የተሰጠው ሆኖ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ሳይኖረው ዕዳውን ያልከፈለ ሆኖ ሲገኝ ፣

(ሐ) የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የተጠየቀበት የታክስ ዕዳ መጠን እንደ ታክስ ከፋዩ አመዳደብ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 ከተቀመጠው አነስተኛ የገንዘብ መጠን በታች ከሆነ ፣

2/ ታክስ ከፋዩ፡

(ሀ) ለዕዳው ማስከፈያ ሀብቱ እንዲያገ ዝ የዕግድ ትዕዛዝ የተላለፈበት ከሆነ ፣

(ለ) በዕዳው የተያዘበትን ንብረት ለመሸጥ የጨረታ ማስታወቂያ የወጣበት ከሆነ ፣

የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የሚሰጠው ለዕዳው ተመጣጣኝ የሆነ የባንክ ወይም የንብረት ዋስትና ሲያቀርብ ብቻ ይሆናል፡፡

አበረ አበበ ሚኒስትር

## 6. ለታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ማመልከቻ መልስ ስለመስጠት

በዚህ መመሪያ መሰረት በቀረበ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ማመልከቻ ላይ የታክስ ባለሥልጣኑ የሰጠውን ውሳኔ የሚገልፅ የጽሁፍ ማስታወቂያ ማመልከቻው በቀረበ በ 30 ቀናት ውስጥ ለታክስ ከፋዩ መስጠት አለበት፡፡

# ክፍል ሦስት

## የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስለሚፈቅደው አካል ፣ የመክፈያ ጊዜና አከፋፈሉ

## 7. የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነትን ስለሚፈቅደው አካል እና የጊዜ ገደብ ስለመወሰን

1/ በአንቀጽ 8 የተመለከተው ቢኖርም ታክስ ከፋዩ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከዝቅተኛው የታክስ ዕዳ መጠን በታች ሆኖ ታክስ ከፋዩ በአንድ ጊዜ መክፈል የማይችል መሆኑ ከተረጋገጠ የቅ/ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ ለአንድ ጊዜ ከ 3 ወር ሳልበለጠ ጊዜ እንዲራዘምለት ሊፈቅድ ይችላል፡፡

2/ ታክስ ከፋዩ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በራስ ታክስ ስሌት የሚከፍለውን የንግድ ትርፍ ግብር መክፈል አለመቻሉን ጠቅሶ ሲያመለክት የቅ/ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ ጥያቄው በአሳማኝ ማስረጃ ተደግፎ የቀረበ መሆኑን በማረጋገጥ ከ 3 ወር ሳልበለጠ ጊዜ እንዲራዘምለት ሊፈቅድ ይችላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው ቢኖርም ታክስ ከፋዩ ለ3 ተከታታይ የግብር ዘመን ተመሳሳይ ጥያቄ የሚያቀርብ ከሆነ የታክስ ማራዘሚያ ጊዜ ሊፈቀድለት አይችልም፡፡

4/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የ3 ወር ጊዜው መቆጠር የሚጀምረው በታክስ ከፋዩ ማመልከቻ ቀርቦ በስራ አስኪያጅ ውሳኔ ካገኘበት ቀን ቀጥሎ ባለው ቀን ነው፡፡

አበረ አበበ መንገሻ
የሚኒስትር ሕግ አማካሪ

8. የታክስ ዕዳ የመክፈያ ጊዜ ስለመወሰን

ታክስ ከፋዩ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ደርሶት በዚህ መመሪያ መሰረት የታክስ ክፍያ ማራዘሚያ ጊዜ ስምምነት ውል ሲገባ የዕዳው የመክፈያ ጊዜ የሚወሰነው በሚከተለው አግባብ ይሆናል፡፡

1/ በከፍተኛ ታክስ ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች የሚፈለግበት ጠቅላላ ፍሬ ታክስ ፣ ወለድ እና መቀጫ የታክስ ዕዳ፡-

(ሀ) ከብር 1,500,000 /አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ/ እስከ 5,000,000 /አምስት ሚሊዮን/ ከሆነ እስከ 6 ወር ፣

(ለ) ከብር 5,000,001 /አምስት ሚሊዮን አንድ/ እስከ ብር 9,000,000 /ዘጠኝ ሚሊዮን/ ከሆነ እስከ 8 ወር ፣

(ሐ) ከብር 9,000,001 /ዘጠኝ ሚሊዮን አንድ/ እስከ 15,000,000 /አስራ አምስት ሚሊዮን/ ከሆነ እስከ 10 ወር ፣

(መ) ከብር 15,000,001 /አስራ ስምንት ሚሊዮን አንድ/ በላይ ከሆነ እስከ 12 ወር ፣

የክፍያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2/ በመካከለኛ ታክስ ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች የሚፈለግበት ጠቅላላ ፍሬ ታክስ ፣ ወለድ እና መቀጫ የታክስ ዕዳ፡-

(ሀ) ከብር 500,000 /አምስት መቶ ሺ/ እስከ ብር 1,500,000 /አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ/ ከሆነ እስከ 3 ወር ፣

(ለ) ከብር 1,500,001 /አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ. አንድ/ እስከ 3,000,000 /ሦስት ሚሊዮን/ ከሆነ እስከ 6 ወር ፣

(ሐ) ከብር 3,000,001 /ሦስት ሚሊዮን አንድ/ እስከ 4,750,000 /አራት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ/ ከሆነ እስከ 8 ወር ፣

(መ) ከብር 4,750,001 /አራት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ. አንድ/ እስከ ብር 6,000,000 /ስድስት ሚሊዮን/ ከሆነ እስከ 10 ወር ፣

(ሠ) ከብር 6,000,000 /ስድስት ሚሊዮን/ በላይ ከሆነ 12 ወር ፣

የክፍያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፡፡

አበረ አበበ መንገ
የሚኒስትር ሕግ አ.

3/ በአነስተኛ ታክስ ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች የሚፈለግበት ጠቅላላ ፍሬ ታክስ ፣ ወለድ እና መቀጫ የታክስ ዕዳ፡-

(ሀ) ከብር 50,000 /ሀምሳ ሺ/ እስከ 100,000 /አንድ መቶ ሺ/ ከሆነ እስከ 3 ወር ፣

(ለ) ከብር 100,001 /አንድ መቶ ሺ. አንድ/ እስከ ብር 350,000 /ሦስት መቶ ሃምሳ ሺ/ ከሆነ እስከ 6 ወር ፣

(ሐ) ከብር 350,001 /ሦስት መቶ ሃምሳ ሺ. አንድ/ እስከ ብር 750,000 /ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ/ ከሆነ እስከ 8 ወር ፣

(መ) ከብር 750,001 /ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ. አንድ/ እስከ 2,000,000 /ሁለት ሚሊዮን/ ከሆነ እስከ 10 ወር ፣

(ሠ) ከብር 2,000,000 /ሁለት ሚሊዮን/ በላይ ከሆነ እስከ 12 ወር ፣

የክፍያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፡፡

4/ በጥቃቅን ታክስ ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች የሚፈለግበት ጠቅላላ ፍሬ ታክስ ፣ ወለድ እና መቀጫ የታክስ ዕዳ፡-

(ሀ) ከብር 10,000 (አስር ሺ.) እስከ 25,000 (ሃያ አምስት ሺ.) ከሆነ እስከ 3 ወር፣

(ለ) ከብር 25,001 (ሃያ አምስት ሺ. አንድ) እስከ 50,000 (ሃምሳ ሺ.) ከሆነ እስከ 6 ወር ፣

(ሐ) ከብር 50,001(ሃምሳ ሺ. አንድ) እስከ 75,000 (ሰባ አምስት ሺ.) ከሆነ እስከ 8 ወር፣

(መ) ከብር 75,001 (ሰባ አምስት ሺ. አንድ) እስከ 100,000 (አንድ መቶ ሺ.) ከሆነ እስከ 10 ወር ፣

(ሠ) ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ.) በላይ ከሆነ እስከ 12 ወር ፣

የክፍያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 የተመለከቱት ሁኔታዎች መሟላቱ ተረጋግጦ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የተሰጠው ታክስ ከፋይ ከታክስ ባለስልጣኑ ጋር የክፍያ ጊዜ ስምምነት እንዲፈርም ይደረጋል፡፡

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 በተገለጸው መሠረት የታክስ ዕዳ ፍሬ ታክስ ፣ ወለድ ፣ መቀጫ ያካተተ ከሆነ በአስተዳደራዊ መቀጫ አነሳስ መመሪያ መሠረት የማይነሳው መቀጫ መጠን ብቻ ተሰልቶ የውሉ አካል የሚደረግ ሲሆን ፣ የውሉ አካል ያልሆነው መቀጫ



አበረ አበበ መንገሻ
የሚኒስትር ሕግ አማካሪ

አነሳስ ተፈጻሚ የሚሆነው ፍሬ ታክስ ፣ ወለድና የማይነሳው መቀጫ መክፈሉ ከተረጋገጠ በኋላ ይሆናል፡፡

7/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 መሰረት ታክስ ከፋዩ የመጀመሪያ የክፍያ ስምምነት ውል ተፈራርሞ ግዴታውን ከአቅም በላይ በሆነ በሆነ ምክንያት መወጣት ያልቻለ ሆኖ በድጋሚ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ እንዲሰጠው ከማስረጃ ጋር ጥያቄውን ሲያቀርብ የታክስ ዕዳ አስተዳደር የሥራ ሂደት አስተባባሪ ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ በማቅረብ ውሳኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል፡፡

8/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 መሰረት የቀረበለት የሥራ ኃላፊ ማስረጃውን በመመዘን በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 በተመለከተው የመክፈያ ጊዜ አሰጣጥ ሥርዓት መሰረት የታክስ ዕዳውን እንዲከፍል በድጋሚ ሊፈቅድ ይችላል፡፡ ሆኖም ግን በድጋሚ ተፈቅዶለት ግዴታውን ያልተወጣ ታክስ ከፋይ ሌላ ማራዘሚያ ስምምነት ሊፈቀድለት አይችልም፡፡

9/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 7 እና 8 መሰረት በድጋሚ የክፍያ ማራዘሚያ አገልግሎት የተሰጠው ታክስ ከፋይ ድጋሚ ስምምነት ከሚገባት የታክስ ዕዳ ላይ ቅድሚያ 25 በመቶ መክፈል ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አራት

## የማራዘሚያ ጥያቄ አቀራረብ ፣ መሟላት ያለባቸው የታክስ ዕዳ ክፍያ ማራዘሚያ ቅድመ ሁኔታዎች እና የአፈፃፀም ሥርዓቱ

9. ታክስ ከፋይ ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ፤-

1/ በዚህ መመሪያ መሰረት የክፍያ ጊዜ ስምምነት በሚገባበት የታክስ ዕዳ 25% ቅድሚያ ክፍያ መክፈል አለበት፡፡

2/ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ የቀረበው የታክስ ከፋዩ ሀብት ለዕዳው ማስከፈያ እንዲያገ፤ የዕግድ ትዕዛዝ ከተላለፈበት በኋላ ሲሆን የታክስ ባለሥልጣኑ የታክስ ከፋዩን ሀብት ለመያዝና ለማስተዳደር ያወጣቸው ወጪዎች እና ታክስ ዕዳውን 25% ቅድሚያ ክፍያ መክፈል አለበት፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን ለማስፈፀም ለዕዳው ተመጣጣኝ የሆነ የባንክ ዋስትና ወይም ከዕዳ ነፃ የሆነ ሀብት/ንብረት ያለው መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ካቀረበ እና ይህ ሀብት ከታክስ ባለስልጣኑ ዕውቅና ውጪ በውሉ መሰረት ግዴታውን ተወጥቶ



አበረ አበበ መንገሻ
የሚኒስትር ሕግ አማ..

እስኪጨርስ እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ አሳግዶ ካቀረበ በታክስ ዕዳ ማካካሻነት የተያዘው ንብረት ዕግዱ ሊነሳለት ይችላል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሱትን የቅድሚያ ክፍያ ለመወሰን የስሌት መሠረቱ ፍሬ ታክስ ፣ ወለድና የማይነሳው መቀጫ መጠን ይሆናል፡፡

5/ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ወይም በፍርድ አፈፃፀም ላይ የሚገኝ ሲሆን ታክስ ከፋዩ የታክስ ባለሥልጣኑ የታክስ ዕዳ አሰባሰቡን ለመከታተል ያወጣቸውን ወጪዎች በሙሉ እንደ አግባብነቱ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም 2 ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ጋር በቅድሚያ መክፈል ይኖርበታል፡፡

6/ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ደርሶት በውሳኔው ላይ ባለመስማማት ለታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ የስራ ክፍል ቅሬታውን ሲያቀርብ አምኖ የከፈለው ታክስ ወይም ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም ወደ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቅሬታውን ሲያቀርብ የከፈለው ታክስ የመክፈያ ጊዜ ስምምነት በሚገባበት ጊዜ አስድሞ ከዕዳው ላይ ተቀናሽ ይደረግለታል፡፡ እንዲሁም ከፍርድ በኋላ ስምምነት በሚገባበት ጊዜ በዚህ መመሪያ በተገለፀው መሰረት መስፈርቱን አሟቶ ውሉን ሊፈጽም ይችላል፡፡

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም 2 እና አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 5 ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን እና በመክፈያ ጊዜ የሚፈጸመው የአከፋፈሉ ቅደም ተከተልም በታክስ አስተዳደር አዋጁ አንቀጽ 34 መሰረት ይሆናል፡፡

8/ ቅድሚያ ክፍያ ከተፈጸመ በኋላ ላሉት ቀሪ ክፍያዎች የመክፈያ ጊዜው የሚታሰበው ቅድሚያ ክፍያው ከተፈጸመበት 30ኛው ቀን ላይ ይሆናል፡፡

9/ በዚህ መመሪያ መሠረት የክፍያ ጊዜ ስምምነት የተገባበት የዋና ታክስ ክፍያ መከፈል ከነበረበት ቀን ጀምሮ እስከተከፈለበት ቀን ባለው ጊዜ አዋጁ በተደነገገው ስሌት መሠረት ወለድ ይከፈልበታል፡፡

10/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 የተመለከተውን ለማስፈፀም በዘገየ ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድ ጠቅላላ መጠን በታክስ ከፋዩ ካልተከፈለው ፍሬ ታክስ ታክስ ሊበልጥ አይችልም፡፡

11/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 አፈፃፀም ወለድ የሚታሰበው ባልተከፈለው ወይም በሚቀረው ፍሬ ታክስ ላይ ብቻ ነው፡፡

12/ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የተፈቀደለት ታክስ ከፋይ ስምምነት ገብቶ መክፈል ከጀመረ በኋላ ላለው ጊዜ በአዋጁ አንቀጽ 105 መሰረት ታክስን አዘግይቶ መክፈል የሚያስከትለው ቅጣት አይታሰብም፡፡

13/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 12 ቢኖርም ታክስ ከፋይ በገባው የክፍያ ጊዜ ስምምነት መሰረት



ለበረ ለበበ መንገሻ
የሚኒስትር ሕግ ለማገ

መክፈል ያለበትን የታክስ ዕዳ ሳይከፍል ያቋረጠ እንደሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 12 ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

10. የኤሌክትሮኒክ ዘዴን ስለመጠቀም፤

ሀ) ታክስ ከፋዩ የታክስ ክፍያ ማራዘሚያ ለመጠየቅ የሚቀርበውን ማመልከቻ የኤሌክትሮኒክ ዘዴን በመጠቀም ሊያቀርብ ይችላል፡፡

ለ) ባለስልጣኑ ፈቃድ በቀረበለት የክፍያ ማራዘሚያ ጥያቄ ላይ ምላሽ ለመስጠት፣እና ከዚሁ ገዳይ ጋር በተያያዘ ከታክስ ከፋይ ጋር የሚደርጋቸውን ሌሎች ግንኙነቶች የኤሌክትሮኒክ ዘዴን በመጠቀም ሊያከናውን ይችላል፡፡

11. <u>በልዩ ሁኔታ የሚሰጥ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ</u>

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4፤ 5 ፣ 7 ፣ 8 እና 9 ላይ የተመለከተው ቢኖርም ታክስ ባለስልጣኑ በልዩ ሁኔታ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2/ በልዩ ሁኔታ የመክፈያ ጊዜ እንዲራዘም የሚቀርቡ ጥያቄዎች የሚቀርቡት ለቅ/ጽ/ቤቱ ይሆናል፡፡

3/ ቅ/ጽ/ቤቱ ከታክስ ከፋዩ የሚፈለግ ጠቅላላ የታክስ ዕዳ መጠን ፣ የታክስ ዓይነት ፣ የታክስ ዕዳው ያለበት ሁኔታ (Status) ፣ የታክስ ከፋዩ አከፋፈል ታሪክ ፣ በልዩ ሁኔታ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የተጠየቀበትን ተጨባጭ ምክንያት (ማስረጃ) እና ከታክስ ከፋዩ ጥያቄ አንጻር የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን ዝርዝር የውሳኔ ሀሳብ በሥራ አስኪያጁ ተፈርሞ ለታክስ ዕዳ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ይልካል፡፡

4/ የታክስ ዕዳ አስተዳደር ዳይሬክቶሬቱ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤት የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ መርምሮ ለሚኒስትሩ ወይም ሚኒስትሩ ለወከለው የሥራ ኃላፊ የውሳኔ ሀሳብ አቅርቦ በሚወሰነው መሰረት እንዲፈፀም ለቅ/ጽ/ቤቱ መልሶ ያስተላልፋል፡፡

5/ ሚኒስትሩ ወይም ሚኒስትሩ የወከለው የሥራ ኃላፊ የክፍያ ስምምነት ለገባ ታክስ ከፋይ ያለበትን የዕዳ ጫና ከግምት ውስጥ በማስገባት የቅድሚያ ክፍያውን እስከ 15 በመቶ ዝቅ ሊያደርግ ይችላል፡፡

6/ ይህ አንቀጽ ለአዲስ አበባ እና ለድሬዳዋ አስተዳደር ገቢዎች ባላስልጣንን በተመለከተ በተመሳሳይ ደረጃ ባሉ ኃላፊዎች ይፈጸማል፡፡

አበረ አበበ መንገሻ
የሚኒስትር ሕግ አማካሪ

12. <u>የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ አቀራረብ፣ ስለሚፈቅደው አካል እና አፈፃፀም ሥርዓት</u>

1/ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ የታክስ ዕዳውን አጠቃሎ በአንድ ጊዜ የመክፈል አቅም የሌለው መሆኑን ገልጾ ጥያቄውን ለቅ/ጽ/ቤቱ የታክስ ዕዳ አስተዳደር የስራ ክፍል ሲያቀርብ እና ምክንያቱ ተቀባይነት ሲያገኝ በዚህ መመሪያ በተገለፀው ሁኔታ የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

2/ ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረበ የክፍያ ጊዜ ስምምነት ከሆነ የታክስ ዕዳ አስተዳደር የስራ ክፍል በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 በተመለከተው መሰረት የክፍያ ጊዜ ስምምነት ሊፈቅድ ይችላል፡፡

3/ በድጋሚ የቀረበ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ከሆነ የታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ስራ አስኪያጅ የሚፈቅድ ይሆናል፡፡፡

4/ በአንቀጽ 7 (1) ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስን አንቀጽ 2 እና 3 እንዲሁም በአንቀጽ 11 መሰረት ታክስ ከፋዩ ያቀረበው የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ተቀባይነት ካገኘ በቅ/ጽ/ቤቱ ለሥራው አግባብነት ያለው የታክስ ዕዳ አስተዳደር ባለሙያ የስምምነት ውል በማዘጋጀት ለሥራ ሂደት መሪው አቅርቦ እንዲፈረም ያደርጋል፡፡

5/ የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል በ 3 ኮፒ ተዘጋጅቶ ዋናው ኮፒ ከማህደር ጋር ይያያዛል ፣ 2ኛው ኮፒ ለግብር ከፋዩ ይሰጣል ፣ 3ኛው ኮፒ በታክስ ዕዳ አስተዳደር ስራ ሂደት ለቀጣይ የክትትል ስራ የሚያገ ይሆናል፡፡

6/ በክፍያ ጊዜ ስምምነት ውሉ መሠረት ክፍያ የሚፈጸምበት ቀን በበዓላት ወይም በዕረፍት ቀናት ላይ ከዋለ ክፍያው በቀጣዩ የስራ ቀን መፈጸም አለበት፡፡

7/ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የጳጉሜ ወር የነሐሴ ወር አካል ሆኖ ይቆጠራል፡፡

8/ የታክስ ዕዳ አስተዳደር የሥራ ክፍል የክፍያ ጊዜ ስምምነት የገቡ ታክስ ከፋዮችን ዝርዝር ፣የክፍያ ስምምነት የተገባበትን የታክስ ዓይነት ፣ የታክስ ዘመን ፣ ፍሬ ታክስ ፣ መቀጫ እና ወለድ ፣ በቅድሚያ የተከፈለ ገንዘብ መጠን ፣ ስምምነት የተገባበት ቀን እና የመክፈያ ጊዜ ያካተተ ሪፖርት በየወሩ እያዘጋጀ ለዋና መ/ቤት የታክስ ዕዳ አስተዳደር የስራ ክፍል ይልካል፡፡

13. <u>የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል ግዴታን አለመፈጸም</u>

1/ በዚህ መመሪያ መሠረት የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የተፈቀደለት ታክስ ከፋይ በውሉ መሠረት በየወሩ ካልከፈለ የስምምነቱ መሰረዝ እንደተጠበቀ ሆኖ ታክስ ከፋዩ ክፍያውን ካቆመበት ጊዜ አንስቶ ያልተከፈለዉን ቀሪ ዋና ታክስ ፣ ወለድ እና መቀጫ ተሰልቶ በሙሉ እንዲከፍል የታክስ ባለሥልጣኑ በታክስ ህጉ መሰረት እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡



ሳህሬ ሳበበ
የሚኒስት..

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ታክስ ከፋዩ ክፍያ ያቋረጠው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ ከተረጋገጠ አቋርጦት የነበረውን ታክስ በስምምነት ውል ጊዜ ውስጥ ያልከፈለባቸውን ወራት አጠቃሎ እና የወጡ ወጪዎችን ጨምሮ የከፈለ ከሆነ የስምምነቱ ውል ወቅታዊ ተደርጎ ሳይሰረዝ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

14. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በነበረዉ መመሪያ ተቀባይነት አግኝቶ በታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ውል መሰረት በመከፈል ላይ ያለ የታክስ ዕዳ በነበረው መመሪያ መሠረት ተፈጻሚነቱ ይቀጥላል፡፡

15. ስለተሻሩ መመሪያዎች

የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የሚቃረኑ ማናቸውም ሰርኩላሮችና አሰራሮች እንዲሁም የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ መመሪያ ቁጥር 142/2011 በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

16. መመሪያው የሚፀናበት ቀን

ይህ መመሪያ በሚኒስትሩ ጸድቆ በሚኒስቴሩ ድህረ ገፅ ላይ ከተጫነበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ

ጥር 2015 ዓ.ም

አይናለም ንጉሴ ዓሊ
ሚኒስትር

ዓይናለም ንጉሴ ዓሊ

የገቢዎች ሚኒስቴር

ሚኒስትር

አበረ አበበ መን
የሚኒስትር ሐግ